# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## በዩትሬክት ሆላንድ ስለተካሄደው ስብሰባ
## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የተሰጠ ልዩ መግለጫ

ሕዝባችንን በኢሕአዴግ አሸባሪ አገዛዝ እየደረሰበት ካለው ሁለ-ገብ ወከባ ለማዳንና አገራችን ኢትዮጵያን ከምትገኝበት አጣብቂኝ የፖለቲካ ቀውስ ለማውጣት አገዛዙን ተቃውመው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ስብስቦች በጋራ መሥራታቸውና ትግላቸውን ማቀናጀታቸው እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ከምሥረታው ጀምሮ አስተማማኝ፥ እውነተኛ፥ ቀናና የሕዝብንና የአገርን ጥቅም የሚያስጠብቅ ብሐራዊ ስብስብ እንዲፈጠር በግንባር ቀደምትነት ሙከራዎችን ከማድረግ አልተቆጠበም፡፡ በዚህ ረገድ ተግባራዊ የጋራ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲቻል ላቀረብነው ተደጋጋሚ ጥሪ በጎ ምላሽ ከሰጡ ወገኖች ጋር ሃሳባችን ተግባራዊ እንዲሆን ተከታታይ ውይይቶችን አድርገናል፡፡

ከግንቦት ፲፩ ቀን እስከ ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም (ሜይ 19- 22, 2006) በሆላንድ አገር ዩትሬክት ከተማ በኦነግ በተጠራው ስብሰባ ላይ ኅብረታችን የተገኘው ከዚሁ መሠረታዊ እምነት በመነጨ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ስብሰባ ሁሉን ባካተተ መልክ እንዴት፥ መቸና የት መደረግ እንዳለበት ከኦነግ ጋር በቅርብ እየተመካከርንና መሠረታዊ መግባባት ላይ እያለን ስብሰባው ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ሲቀር በግንበት ፬ ቀን ፺፰ ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በተጠቀሰው ስብሰባ ላይ እንድንገኝ ጥሪ ሲደርሰን ምንም እንኳን ይኸ አጠራር መደበኛ የስብሰባ አካሄድ ሥርዓትን ያልተከተለና ከነበረን የጋራ ጥረት ለየት ያለ ቢሆንም የተሰማንን ቅሬታ በቃልም በደብዳቤም ገልፀን፥ በእኛ በኩል ምን ጊዜም መቅደም ያለበት የአገርና የወገን ጉዳይ በመሆኑ በስብሰባው ለመገኘት ወስነን ተገኝተናል፡፡

ስብሰባው የተጠራው ቀደም ሲል ኅብረቱ ባቀረበው ሃሳብ መሠረት እንደሆነ፥ የመጀመሪያ ደረጃ (preliminary) ስብሰባ እንደሆነ፥ አጀንዳም እዚያው ስብሰባ ላይ የሚነደፍ መሆኑን አዘጋጅው ክፍል በቃልም በጽሑፍም ስላረጋገጠልን፥ የዚህ ዓይነት መሰባሰብ ሁሉን-አቀፍ፥ አጀንዳውም ግልጽ መሆን እንደሚገባውና እርባና ያለውና መሠረቱ የጠና የጋራ የትግል መድረክ ስለሚፈጠርበት ሂደት ያለውን መተክላዊ አቋምና አመለካከት በጽሑፍ አቅርቦ፥ በወኪሎቹ አማካይነትም እንዲገለጽ በቀና መንፈስ በማሰብ እስከሚቻል ድረስ ኅብረታችን በስብሰባው ተካፍሏል፡፡

ኅብረታችን ይኸ ስብሰባ መካሄድ በመቻሉ ደስተኛ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የሚያርጉት መሰባሰብ ምን ጊዜም ሊበረታታ ይገባል፡፡ በጣም የተራራቀ አስተሳሰብና የማይጣጣም አቋም ያላቸው ኃይሎች አንድ ላይ መሰብሰብ መቻላቸው እራሱ አዎንታዊ ግኝትና ወደፊትም ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው፡፡ እኛም በቦታው የተገኘነውና ስብሰባው መልካም ፍሬ ይዞ እንዲወጣ ጥረት ያደረግነው የተለያዩ አስተሳሰቦችን ይዞ በልዩነት አብሮ መሥራት ይቻላል ከሚለው መሠረታዊ እምነት በመነጨ አመለካከት ነው፡፡ ይሁንናም ስብሰባው አስቀድሞ ለብቻ በተዘጋጀ አጀንዳ ላይ ብቻ ያተኮረና ምንም ዴሞክራሲያዊነት በሌለው አካሄድ ቀደም ሲል ያለቀ ውጤት ይዞ ለመውጣት የታቀደ ሆኖ በመገኘቱ ከልብ አዝነናል፡፡

ኅብረታችን የሚታገለው በጠራ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ፥ ሁሉን-አቀፍ፥ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብሔራዊ ሉአላዊነት የጠበቀ ስብስብ በመፍጠር

ኅብረተሰባችንን በሰከነ ሽግግር ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የሚወስድ ሁኔታን ለማመቻቸት ነው።

ይኸ ስብሰባ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ከዚህ መሠረታዊ አስተሳሰብ የወጣ ሆኖ ስላገኘነው ኅብረቱ በዚህ ስብሰባ ፍጻሜ ላይ ተፈጠረ የተባለው ስብስብ መሥራችም፥ አባልም ሆነ አካል እንዳልሆነ እናስታውቃለን።
ስለ ስብሰባው ሂደትም ሆነ በኅብረቱ ስለቀረቡ ሃሳቦች በተከታታይ ይፋ መግለጫዎች ይሰጣሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጋጦ የሚጠብቀው የተቃዋሚ ኃይሎች ስብስብ ለጊዜው ባሰብነው መልክ እውን መሆን ባለመቻሉ ሃዘኔታ ቢሰማንም የሕዝባችንን ትግል ለአዎንታዊ ውጤት ማብቃት እንዲቻል ስህተቶች ታርመው ሁሉን-አቀፍ መሰባሰብ ጊዜ ሳይፈጅ እውን ስለሚሆንበት ኅብረቱ የበኩሉን ጥረት ከማድረግ እንደማይቆጠብ በአክብሮት እንገልጻለን።

ሃቀኛ ትብብር ለአስተማማኝ ድል!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ትግሉ የድሉ ባለቤት ይሆናል።
ድል በኅብረት!!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም